# የአስራ አምስት ቀን ዜና ሚቲዎሮሎጂ

# Met. News








**ቅፅ 8 ቁጥር 8 የህዝብ ግንኙነትና ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት**

**ታህሳስ 2013 ዓ.ም**

# ስልጠናው የትንበያ አቅምን የሚያሳድግ መሆኑ ተገለፀ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መስከረም 2013 በጋራ ለመስራት በተፈራረሙት መሰረት ከብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ 12 እንዲሁም ከኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት 5 በድምሩ ለ17 ሰራተኞች በ REGIONAL CLIMATE MODELING AND ATMOSPHERIC DATA ANALYSIS AND DISPLAY TOOLS በሚል ርእስ ከታህሳስ 5 ቀን 2013 ጀምሮ ሲሰጥ የነበረው የአምስት ቀን ስልጠና አርብ ታህሳስ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ተጠናቀቀ፡፡

የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ክንፈ ኃ/ማሪያም በመዝጊያው ስነስርዓት ላይ እንደተናገሩት የተሰጠው ስልጠና የኤጀንሲውን የትንበያ አቅም ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለውና ቀጣይም እንደዚህ አይነት ስልጠናዎች ለተለያዩ ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ እንደሚሰጥ የገለፁ ሲሆን ከስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ይህንን ኃላፊነት ወስደው በባለቤትነት ሲሰሩ የነበሩትን ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን አመስግነው ሰልጣኞች በአግባቡ እንዲሰለጥኑና በእለት ተእለት ስራቸው ላይ ተግባራዊ እንዲያደርጉ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በስፔስ ሳይንስና አፕሊኬሽን ዲፓርትመንት ውስጥ ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ትጥቁ ካሳ በስልጠናው መጀመሪያ ቀን እንዳሉት የስምምነት ሰነዱ ካሉት ሶስት አላማዎች ውስጥ አንዱ የአቅም ግምባታ ስልጠና በመሆኑ ይህ ስልጠና የስምምነቱ የተግባር ምእራፍ እንደሆነ ተናግረው በስልጠናው የኤጀንሲው የትንበያ አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

በስልጠናው የተሳተፉት የኤጀንሲው ሰራተኞች እንደተናገሩት ስልጠናው እጅግ በጣም ጠቃሚና ለቀጣይ ስራቸው አስፈላጊ መሆኑንና ተከታታይነት ባለው መልኩ መሰጠት እንዳለበት ገልፀው በስልጠናው ላይ ላልተሳተፉት የስራ ባልደረቦቻቸው በስራ ክፍሎቻቸው አማካኝነት እንደሚያሰለጥኗቸው ተናግረዋል፡፡









